EthioLion

# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

# Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፡-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ
**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## ዜና ዘገባ

**ነሐሴ 22 ቀን 2002 ዓ.ም.**

**የወያኔ ስራ አስፈፃሚ የመጨረሻውን ስብሰባ ሊያደርግ ነው**

**ናዝሬት ውስጥ የወያኔ ሊቀመንበር ፤ም/ሊቀመንበር ይመረጣል**

**መለስ አሁንም ይቀጥላል**

**የኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቭዥን ጋዜጠኞች ስራ እየለቀቁ ነው**

**ከበረሀ የመጡ ባለስልጣናትና ዘመዶቻቸው ሀብት እንዳይመዘገብ መለስ ጥብቅ ትዕዛዝ ሰጠ**

ግራ የገባው የኢህአዲግ መንግስት የራሴ ናቸው በሚል ሲያሞካሻቸውና ሲያወድሳቸው የነበሩትን ጋዜጠኞች መልሶ በወር 11 ብር ጭማሪ አደረኩላችሁ እያለ እየተሳለቀባቸው መሆኑ ጋዜጠኞቹ በምሬት ሲገልፁ ተደመጡ።

ሰሞኑን በኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ስር ላሉ ሠራተኞች የደመወዝ ጭማሪ ተደረገ ተብሎ ቢለፍፍም ጭማሪው ሥራና ሠራተኛን ያነጣጠለ ጆሮ ጠቢንና ሠላዮችን ያቆራኘ መሆኑን ጋዜጠኞቹ በምሬት ገልፀዋል።

ልማታዊ ጋዜጠኞች እየተባሉ እየተወደሱ በየክልሉ የፓርቲውን ስራ ብቻ እየሰሩ ሪፖርት ሲያደርጉ የነበሩት እነዚሁ ጋዜጠኞች የደመወዝ ጭማሪ የተደረገላቸው 11 ብር ብቻ መሆኑን ገልፀው

በአንፃሩ ደጋፊ ሆነው ካሜራ ሲቀርፁና በሹፌርነት ተቀጥረው የሚሰሩት እያንዳንዳቸው በወር ከ2 ሺህ ብር በላይ ጭማሪ እንደተደረገላቸው አጋልጠዋል::

እስከ ዛሬ ድረስ አብረን ስንሰራ የስራ ባልደረቦቻችን ይመስሉን ነበር ነገር ግን ለካ ሌላም የስለላ ስራ በተደራቢነት እንደሚሰሩ ዛሬ ነው ያወቅነው ያሉት ጋዜጠኞች ዛሬ የአንድ ተራ ካሜራ ማን ደመወዝ ከ4 ሺህ ብር በላይ ሲሆን የእኛ አለቃ ደግሞ 1 ሺ 8 መቶ ብር ብቻ ነው ሲሉም አጋልጠዋል::

ኢህአዲግን ከህዝብ ጋር እንዲተሳሰር ሌት ተቀን ብርድ፣ ሀሩር፣ ገደል፣ ሜዳ፣ ገጠር፣ ከተማ ሳንል እየተንከራተትን ስንሰራ ኖረን አሁን ግን ይህን የመሰለ ሞራል የሚጐዳ የደመወዝ ጭማሪ ተደረገላችሁ ማለታቸው በእጅጉ የሚያሳፍር ነው ያሉት ጋዜጠኞች ብዙዎቹ ስራቸውን እየለቀቁ መሆኑ ታውቋል::

ነባርና ልምድ ያላቸውን...... ከአለቆቻቸው ጋር የማይስማሙትን...... አሜን ብለው የማይቀበሉትን ጋዜጠኞች የዛሬ ዓመት ገደማ ግምገማ በሚል ሰበብ ያበረሩቸዋው ሲሆን፣ ወጣት የሆኑትን አባብሎ የቀጠራቸው ቢሆንም ሰሞኑን ደግሞ ደመወዝ ተጨመረላችሁ ተብሎ እጅግ በሚያሳዝን ሁኔታ የ11 ብር ጭማሪ መደረጉ ሞራላቸውን ስለነካው ስራቸውን እየለቀቁ ወደ ሌላ ድርጅት እያመለከቱ መሆኑ የታወቀ ሲሆን ለሁሉም መልቀቂያ እንዳይሰጣቸው በረከት ስምኦን እንደከለከላቸው ታውቋል::

በበረከት ሰምኦን የቦርድ ሊቀመንበርነት እየተንቀሳቀሰ ያለው ይሔው መንግስታዊ ድርጅት በህዝብ እና በሀገር ላይ በደል እና ሸፍጥ ሲሰራ አንዳችም ትንፍሽ እንዳይሉ በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ሚስጢሮች ተዳፍነው እንዲቀሩ ተደርጎ ነበር ብለው ያጋለጡት እነዚህ ምሬት የሚያሰሙት ጋዜጠኞች ከእንግዲህ በእጆቻችን የሚገኙትን ምስሎች በተለያዩ ዘዴዎች ለህዝብ እንዲደርስ እና እንዲጋለጥ እናደርጋለን እያሉ እና እየዛቱ መሆኑንም ለማወቅ ተችሏል::

ለኢህአዲግ ባለስልጣናት አጐብድደው ሞያና ክብራቸውን ሸጠው የኖሩት እነዚሁ የኢሀአዲግ የልማት አርበኛ ናቸው የተባሉት ጋዜጠኞች አንድም ለሀገር እና ለህዝብ የሚጠቅም ስራ ሳይሰሩ በአንጻሩ ለወያኔ ሲያጨበጭቡ የቆዩ ቢሆንም ጊዜውን ጠብቆ እንደ አሮጌ ቁና ተሸቀንጥረው ሲወረወሩ ምሬታቸውን ለህዝብ ለመግለፅ መሞከራቸው አሁንም ትዝብት ላይ የሚጥላቸው እንጅ አድማጭ የላቸውም በማለት የአዲስ አበባ ህዝብ በምሬት እየተናገረ ይገኛል::

በበረከት ሰምኦን የበላይነት የተጠናው ይሔው የደመወዝ ጭማሪ በድርጅቱ ውስጥ ሁለት ስራ የተሰጣቸው የስለላ ስራም ካሜራ ማን፣ የሹፌር እና ጆሮ ጠቢነት፣ የመዝገብ ቤት እና የደህንነት ስራን ደርበው ለሚሰሩት ዝቅተኛው የደመወዝ ጭማሪ 2 ሺህ ብር ሲሆን ከፍተኛው እስከ 3 ሺህ ብር መሆኑን ጋዜጠኞቹ አጋልጠዋል::

በዚህም መሰረት የካሜራ ማን እና የሹፌሮች ብሎም ድጋፍ ሰጪ የተባሉ ሠራተኞች ደመወዝ ዝቅተኛው 4 ሺህ ብር የደረሰ ሲሆን የአንድ ነባር ጋዜጠኛ ደመወዝ ደግሞ 1 ሺህ 8 መቶ ብር ብቻ መሆኑንም እያነፃፀሩ የደረሰባቸውን አድልኦ ገልፀዋል::

EthioLion.com

ሠሞኑን ቁጥራቸው የበዙ ጋዜጠኞች የስራ መልቀቂያ ያስገቡ ሲሆን ጥያቄያቸው ተቀባይነት እንደሌለው ሽመልስ ከማል የተሰኘው በልቶ አዳሪ ግለሰብ የገለፀላቸው ቢሆንም ጥያቄ ያቀረቡት በሙሉ ግማሹ የአመት እረፍቱን እየሞላ ሌሎቹም ያለ ፍቃድ በመቅረት ስራ እንዳልገቡ ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የደረሰን ጥቆማ ያስረዳል::

ይሔንኑ የጋዜጠኞች ፍልሰት ለመቋዋቁዋም  በአማራ ክልል ውስጥ ሲሰሩ የነበሩ ነባር ጋዜጠኞች ለመቅጠር እየተሯሯጡ ቢሆንም እነሱም መነሻ ደመወዝ ከ3 ሺህ ብር በላይ ካልሆነ አንቀጠርም በማለታቸው እነ በረከት ሰምኦን ግራ ተጋብተው እንደሚገኙ ምንጮቹ ጠቁመዋል::

የስልጣን እድሜውን በተለያዩ ዘዴዎች ለማራዘም ከፍተኛ ትግል እያደረገ የሚገኘው የኢህአዴግ ቡድን ለመጨረሻ ጊዜ የስራ አስፈፃሚ ስብሰባውን በሚቀጥለው ሳምንት እንደሚያደርግ ታወቀ::

ለአምስት አመታት በስልጣን ላይ የቆየው ይሄው የስራ አስፈፃሚው አካል ተበጥሮ እና ተንገዋልሎ የሚቀጥለው ሊቀጥል የሚራገፈው ሊራገፍ የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጥበት መሆኑን የገለፀው የውስጥ አዋቂ ምንጮች ጥቆማ በዚያው ቀናት ውስጥ አዳዲሶቹ ስራ አስፈፃሚዎች እነ ማን እንደሆኑ የሚታወቁ መሆኑንም ምንጮች ጠቁመዋል::

ከበረሃ ጀምሮ አብረው የመጡት ባለስልጣናትን እያራገፈ መለስ ዜናዊ ብቻውን ስልጣኑን ሙሉ በሙሉ በመቆጣጠር አምስት አመት ሊጓዝ እያመቻቸ መሆኑን የጠቆሙት ምንጮቹ በተለይ በብአዴንና በህወሀት ነባር አመራሮች ላይ ጠበቅ ያለ የማባረር እርምጃ እንደሚወስድ የሚጠበቅ መሆኑን ምንጮቹ ገልፀዋል::

ሠሞኑን ከውስጥ አዋቂ ምንጮች ጥቆማ በደረሰን መሰረት ለ10 ዓመታት በተወካዮች ም/ቤት ተጉልተው የኖሩትን ግለሰቦች እየሾመ ወደ ተለያዩ መስሪያ ቤቶች እየሰገሰጋቸው መሆኑን ጠቁመው ለዚሁ ማሳያ የሚሆነው የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ኮሚሽነሩን ጨምሮ ምክትል ኮሚሽነርና የፋይናንስና ግዥ ፤ደህንነት እና  ጥበቃ መምሪያ ሃላፊዎችን በመለስ ዜናዊ ፊርማ መሾማቸው ታውቆዋል::

አብሲ ሙሜ-ከሐረሪ ብሔራዊ ሊግ፤

-ለገሰ ነጋሽ-ከኦህዴድ፤

-መንግስቱ ቱፋ ከኦህዴድ፤

ዶሰኛው ማሞ-ከብአዴን ከተወካዮች ምክር ቤት ተመርጠው ለሚኒስትር መስሪያ ቤቱ መሾማቸውን የጠቆመው የደረሰን የውስጥ አዋቂ ምንጮች ዘገባ እነሱም ከመለስ በምስጢር  በተሰጣቸው ትእዛዝ መሰረት በመስሪያ ቤቱ አዲስ የምንጠራ ዘመቻ ሊያደርጉ እየሰሩ መሆኑን ገልፀዋል::

EthioLion.com

በህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ውስጥ ለ10 ዓመት ያለ አንዳች ፋይዳ ተጐልተው የኖሩት እነዚሁ የኢህአዲግ አባሎች ዘንድሮ ከምርጫ ተሰርዘው ያልተወዳደሩ በመሆኑ መጪውን አምስት አመት የማረሚያ ቤቱን በበላይነት እንዲመሩ በመለስ ቀጥተኛ ትዕዛዝ የተሾሙ ሲሆን አብረው ያሉ ተያያዥ ጥቅማጥቅሞችም እንዲሰጣቸው በደብዳቤው ተገልፆል፡፡

በዚህ መሰረት አራቱቱ ከተወካዮች ም/ቤት ሲባረሩ ወደ ማረሚያ ቤት የተዛወሩትና የተሾሙት ግለሰቦች ለእያንዳንዳቸው ቪላ ቤት ተፈልጐ እንዲሰጣቸው በመለስ ፊርማ ለአዲስ አበባ መስተዳድር ከንቲካ ኩማ ደመቅሳ መገለፁ ታወቋል፡፡

ዛሬ የአዲስ አበባ ህዝብ በመኖሪያ ቤት እጦት ተቸግሮ ከላይ እታች እያለ እየተንከራተተ ባለበት ......ለልማት በሚል ከቀበሌ ቤቶች እየተፈናቀሉ እየተባረሩ ለጐዳና ህይወት እየተዳረጉ ባሉበት በአሁኑ ወቅት የአህአዲግ ቱባ ባለስልጣናት ከነዋሪው ተነጥቆ እንዲሰጣቸው ከመለስ ዜናዊ በደብዳቤ መገለፁ እንዳሳዘናቸውም ምንጮቹ ገልፀዋል፡፡

በሚቀጥለው ሳምንት ሁሉም ነገር ይጠናቀቃል በተባለለት የኢህአዲግ ስራ አስፈፃሚ ስብሰባ ላይ ቀድሞ ከነበረው 36ቱ ስራ አስፈጻሚ መሀከል ከግማሽ በላይ ተወግዶ በአዲስ እንደሚተካ ቢጠበቅም ዞሮ ዞሮ ውሀ ቢወቅጡት እምቦጭ ነው ሲሉም ሂደቱን ሲከታተሉ የነበሩት የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች ሲገልፁ ተደምጠዋል፡፡

ሌላው የሰሞኑ መነጋገሪያ ሆኖ የሰነበተው የአራቱም ክልሎች ምክር ቤት በአዲስ ተመራጮች የተመሰረተ ቢሆንም እስከ ዛሬ ኘሬዘዳንቶቻቸውን መርጠው ይፋ አለማድረጋቸው የታወቀ ሲሆን ለመለስም ትልቅ ፈተና ከመሆኑም በተጨማሪ አጣብቂኝ ውስጥ እንደከተተው ለመረዳት ተችሏል፡፡

በሚቀጥለው ወር መባቻ ላይ አዲሱ የወያኔ ምክር ቤት 8ኛ ጠቅላላ ጉባኤ የሚካሂድ ሲሆን ይሄንንም ለማዘጋጀት አስቀድሞ ኮሚቴ ተዋቅሮ እየሠራ መሆኑን ሰሞኑን ጋዜጣዊ መግለጫ የሰጠው የጽ/ቤቱ ኃላፊ ሙክታር ከድር የተባለው ጀሌ ግለሰብ ገልፆል፡፡

በተለይ የፊታችን ሳምንት የሚጠናቀቀው የስራ አስፈፃሚ ስብሰባ ከተጠናቀቀ በኂላ ከመስከረም 5 እስከ 7 ቀን 2003ዓ.ም በናዝሬት በሚደረገው ጠቅላላ ጉባኤ ላይ የስራ አስፈፃሚው የወያኔን ሊቀመንበር፣ ምክትል ሊቀመንበርና ሌሎችንም የፓርቲውን ኃላፊዎች የሚመረጡ ሲሆን፣ ይህም ከዚህ ቀደም እንደተደረገው ሁሉ አስቀድሞ ማን ማን መመረጥ እንዳለበት በሚሰጣቸው ትዕዛዝ መሠረት የሚጠናቀቅ መሆኑን ከውስጥ አዋቂ ምንጮች ጥቆማ ለመረዳት ተችሏል፡፡

በወያኔ ውስጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ እርስ በራስ መናናቅ እና መሻኮቱ እየከፋ የመጣ በመሆኑ መተማመን ጠፍቶ በጐጥና በሰፈር ልጅ አልፎ ተርፎ አብሮ በመማር ላይ የተመሰረተ ግንኙነት እየሰፋ በመምጣቱ ለእነ መለስ ዜናው የውስጥ ችግሩ መስፋፋት ከፍተኛ የስጋት አቅጣጫ ሆኖባቸው ይገኛል፡፡

EthioLion.com

EthioLion

ኢህአዴግ ከ30 ዓመት በላይ የአራት ጥምር (ግንባር) ፓርቲ ሆኖ የሰራ ሲሆን ይህንኑ ግንባር ወደ ውሁድ ፓርቲነት ለመቀየር የፓርቲው አባላት ጥያቄው የተነሳ ቢሆንም እነ መለስ ተውጠው የሚቀሩ ስለመሰላቸው ፓርቲው (ቡድኑ) በግንባርነት እንዲቀጥል መደረጉም ታውቋል፡፡

በመጪው መስከረም በናዝሬት በሚደረገው የወያኔ ምክር ቤት ምርጫ እና ጠቅላላ ጉባኤ ላይ የእርስ በርስ ሽኩቻው ገሀድ ወጥቶ ሊያፈጥ ይችላል በሚል ስጋት የገባው የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ከአህዴድ ብሎም ከደአህዴን ውስጥ ያሉ ቁልፍ ሠዎችን መልምሎ ያደራጀ ከመሆኑም በተጨማሪ በሚደረገው የፓርቲዎች ሊቀመንበርነት ምርጫ ላይ ችግር እንዳይፈጠር ከወዲሁ ስራውን ያጠናቀቀ መሆኑንም የደረሰን ጥቆማ ያስረዳል፡፡

ከዚህ ቀደም እንደሆነው ሁሉ የወያኔው ፓርቲ የስልጣን መዋቅር

ሊቀመንበር ከህወሀት መለስ ዜናዊ

ም/ሊቀመንበር ከብአዴን

ፀኃፊ ከኢህዴድ

የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ ከአኢህዴን ተብሎ ከወዲሁ ተሰርቶ ያለቀ ሲሆንና በጉባኤው ወቅት ይሄው አስቀድሞ የተሰራው መዋቅር ይፋ ይሆናል ሲልም የደረሰን ጥቆማ ያብራራል፡፡

በተለይ የሚመረጡት አዲሶቹ ስራ አስፈፃሚዎች መካከል ችግር እንዳይፈጠር መለስ ዜናዊ በግሉ እየጠራ እያነጋገረና እያስፈራራ መሆኑን የጠቆመው የደረሰን ዘገባ ከወዲሁ በመካከላቸው ችግር ይፈጠራል የሚል ስጋትና ጭንቀት ስለፈጠረበት በከፍተኛ ሁኔታ እየተሯሯጠ እንደሚገኝም የደረሰን ዘገባ ገልጿል፡፡ይሄንን የመለስ ዜናዊ ጭንቀት የተከታተሉ አንዳንድ የፖለቲካ ተንታኞች እንደሚሉት ከሆነ የወያኔ ስርዓት ውድቀት የሚጀምረው ከመጪው መስከረም ጀምሮ ነው ሲሉም ተደምጠዋል፡፡

በተከታታይ ለአምስት አመታት ሁለት አህዝ ያለው እድገት አስመዝግቤያለሁ እያለ ሲለፍፍ የነበረው የወያኔ ቡድን በቅርቡ ደግሞ ዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን በሚል ህዝብን ሊያታልል ባዘጋጀው ዕቅድ ላይ ህዝብን ከችግር አላቅቃለሁ እያለ እያናፋ ቢገኝም በአሁኑ ሠዓት በሀገሪቱ ዜጐች ላይ እየደረሰ ያለውን ሰቆቃ መታደግ እንዳልቻለና ፍላጐትም እንደሌለው የደረሰን ዘገባ ገለፀ፡፡

ሰሞኑን በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ተፈጥሮ ባስከተለው ችግር ምክንያት ቁጥራቸው የበዛ ዜጐች ለህልፈተ ህይወት የተዳረጉ ሲሆን ለከፉ ጉዳት እና ለጉዳና ህይወት እየተዳረጉ እንደሆነም ታውቋል፡፡

በተለይ በአማራ ክልል በወሎ ክፍለ ሀገር ውስጥ በተከታታይ የደረሰ የተፈጥሮ አደጋ ምክንያት እጅግ ብዙ ዜጐች ለሞት የተዳረጉ ከመሆኑም በተጨማሪ ብዙ ሰዎችም የደረሱበት ጠፍተው እንዳሉም የደረሰን ዘገባ ገለፆ እሁድ ሐምሌ 16 ቀን 2002ዓ.ም ከሌሊቱ 9 ሠዓት የመርሳ ከተማ አቅራቢያ አባይ ተራራ ተንዶ 15 ሰዎች ወዲያውኑ ሲሞቱ ከ30 በላይ ከባድ ጉዳት እንዳደረሰባቸው ከደረሰን ዘገባ ለመረዳት ተችሏል፡፡

ከወልዲያ 40 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የምትገኘው መርሳ ከተማ በደረሰው ድንገተኛ አደጋ ከሞቱት እና ጉዳት ከደረሰባቸው ሰዎች በተጨማሪ በደለል ተሸፍነው የተደበቁና የደረሱበት ያልታወቁ ዜጐችም ብዙ መሆናቸውን ከመርሳ ነዋሪዎች የደረሰን ጥቆማ አጋልጧል።

በለፈው ሳምንት ውስጥ በከሚሴ በደረሰው የጐርፍ አደጋ ቁጥራቸው ያልታወቀ ሠዎች በውሀ ተወስደው የሞቱ ከመኖራቸውም በተጨማሪ በመጠለያ እጦት ህፃናት እና አዛውንቶች መሞታቸው ተዘግቧል።

ከ10 ሺ ሠዎች በላይ ተፈናቅለው ያሉበትን የከሚሴን ችግር ዞር ብለው ያላዩት የወያኔ ባለስልጣናት እንደገና በመርሳ ከተማ ለተፈጠረው ችግር ትኩረት ሳይሰጡት አንዳችም ድጋፍና እርዳታ ሳይደረግላቸው በችግር ላይ ችግር ተደራርቦባቸው ይገኛሉ።

የተበላሸና የሻገተውን ፖለቲካ ብቻ ለማቆየት እና እድሜውን ለማራዘም በሚል በመቶ ሚሊዮን ብሮች እየመነዘረ ያለው የወያኔ ቡድን በችግር ላይ ላሉ የሀገሪቱ ህዝቦች አንዳችም ትኩረት ካለመስጠቱም በላይ አደጋው መከሰቱን የሀገር ውስጥ መገናኛዎች እንዳይገልፁ መከልከሉ ታውቋል።

በሌላ በኩል የአዋሽ ወንዝ በመሙላቱ በዙሪያው ያሉ ዜጐች ተፈናቅለው ቀዬአቸውን እየለቀቁ ወደ ከተማ ከመግባታቸውም በላይ የሚቀምሱት በማጣታቸው ለልመና ተዳርገዋል። ለስሙ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ተብሎ የተቋቋመው ድርጅት ከውጭ ሀገር መንግስታት እላ ከለጋሽ ድርጅቶች በህዝቡ ስም የተሰጠውን እርዳታ እህል እየቸበቸበ ለጦር መሳሪያ እያዋለው በመሆኑ በአሁኑ ሠዓት አንዳችም ድጋፍ ሊያደርግ አለመንቀሳቀሱም ታውቋል።

በመጨረሻም ለዓመታት በወሬ ደረጃ እየተወራ እና እየተናፈሰ የቆየው የባለስልጣናት ሀብት መመዝገብ ሠሞኑን በአዲስ መልክ እንደገና አሁንም ሊጀመር ነው ተብሎ መግለጫ እየተሰጠበት ይገኛል።

ይሔው የባለስልጣናትን እና ዘመዶቻቸውን ሀብት ምንጭና ከየት እንደተገኘ ለመመዝገብ የሚያስችል ዝግጅት ተጠናቋል እያለ የሚያናፋው በመለስ ቁጥጥር ስር ያለው የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከ50 ሺህ በላይ የሆኑትን በቅርቡ እንመዘግባለን እያለም መግለፁ ታውቋል።

ምንም እንኳን የባለስልጣናትን ሀብትና የቅርብ ዘመዶቻቸውን ጭምር እንመዘግባለን ተብሎ እየተወራና መግለጫ እየተሰጠበት ቢሆንም ከበረሀ የመጡት ቱባ ባለስልጣናትና በመከላከያ ውስጥ የሚሰሩ ጄኔራሎች እንዳይነኩ ከበላይ ተቆጣጣሪው መለስ ዜናዊ ለፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ጥብቅ ትዕዛዝ የተሰጠ በመሆኑ ትኩረቱ ከከተማ እንደ እንጉዳይ በፈለቁት ግልገል ሹማምንቱ ላይ ብቻ የሚያነጣጥር መሆኑ ታውቋል።

ከወረዳ እስከ ዞን ብሎም ቀበሌና ክፍለ ከተማ ድረስ ያሉ ሹማምንቶችንና የቅርብ ዘመዶቻቸውን ሀብት እንዲመዘገብና ሌሎችም በኑሮ ደረጃ ዝቅተኛ የሆኑ አስፈፃሚ አካላት የሚባሉት ዳኛ፣ አቃቤ ህግና ትራፊክ ፖሊስ፣ የጣቢያ አዛዥ ፖሊሶች እና የመሳሰሉት ግንባር ቀደም ተጠቃሽ መሆናቸውን የውስጥ አዋቂ ምንጮች ጥቆማ አጋልጧል።

EthioLion.Com

የሀገሪቷን ሀብትና ንብረት ከእግር ጥፍራቸው እስከ ራስ ፀጉራቸው ድረስ ግጠውና አከማችተው ከጨረሱ በኋላ ዛሬ እንደ አዲስ ሀብት ምዝገባ እያሉ ህዝብን ለማታለል ቢጥሩም ህዝቡ አስቀድሞ የተረዳው በመሆኑ ሊያታልሉት እንደማይችሉ በገሀድ እየነገራቸው ይገኛል፡፡

ዛሬ አንድ የወያኔ ጦር አዛዥ ጄኔራል መኮንን ከሁለት መኖሪያ ቪላዎች በተጨማሪ የሚያከራየው ባለ 5 እና ከዛም በላይ ህንፃ አሰርቶ የሚገኝ መሆኑን የገለፁት የውስጥ አዋቂ ምንጮች ከበረሀ የመጡ የወያኔ ባለስልጣናትም ቢሆኑ እያንዳንዳቸው ከኢትዮጵያ ህዝብ ጉሮሮ ላይ እየነጠቁ አንቱ የተባለ ሀብት ያካበቱ ከመሆኑም በተጨማሪ ማንበብና መፃፍ የማይችሉ ከገጠር ለመጡ ዘመዶቻቸው ኩባንያዎችን አቋቁመው እየሰሩ መሆኑ እየታወቀ ምዝገባው እነሱን አይመለከትም ተብሎ በመለስ ትዕዛዝ መሰጠቱ እየተደረገ ያለው ቀልድና ጨዋታ መሆኑ ግልፅ ነው ሲሉ የሀገሪቱ ህዝቦች በቁጭት እየገለፁ ይገኛሉ፡፡

የራሱ የመለስ ዜናዊ ባለቤት አዜብ መስፍን ከ10 በላይ ግዙፍ ኩባንያዎችን መስርታ በበላይነት እያንቀሳቀሰች ከመሆኑም ባሻገር መንግስታዊ ዕቃ ግዥ ሲፈፀም ኮሚሽን እየተቀበለች የሀገሪቱን ህዝብ እርቃኑን ያስቀረች ሙሰኛ መሆንዋን በማወቁ ሚስቱን ለማዳን ሲል ጠቅላላ ከበረሀ የመጡ ባለስልጣናት እንዳይመዘግቡ ......እንዳይከሰሱ........ እንዳይወቀሱ...... በማለት ትዕዛዝ መስጠቱ ተጋልጧል፡፡

በመኪና አስመጪነት፣ በአበባ እርሻ ኢንቨስትመንት፣ በሰሊጥ እና ቡና ላኪነት፣ በመንገድና ህንፃ ግንባታ ኮንትራክተርነት፣ በመንግስታዊ መ/ቤቶች ዕቃ ግዥ ኮሚሽን ተቀባይነት እና በመሳሰሉት ግዙፍ የንግድ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ተዘፍቃ የምትገኘው አዜብ መስፍን የኢትዮጵያ ህዝብ እና የሀገሪቷን ሀብት አግበስብሳ ያካበተች መሆኑ ግልፅ እና ግልፅ በመሆኑ እሷን ለማዳን ሲል የበረሀ ጓደኞቹን በሙሉ እሱ እስካለ ድረስ እንዳይጠየቁ ማድረጉ ታውቋል፡፡

ከበረሃ መጥተው አራት ኪሎ ቤተ ጥሞንግድት ሲገቡ ሁሉም ባለ 8 ቀዳዳ ጉማ ጫማና ታጣፊ ራሽያ ሠራሽ ክላሽን ብቻ የነበራቸው ቢሆንም ዛሬ ግን እያንዳንዳቸው ከኩባንያ እስከ ባለ 4 ኮከብ ሆቴል ባለቤትነት......ከደረቅ ጭነት ማመላለሻ እስከ ፍሳሽ መጫኛ ቦቲ ባለንብረት......ከቪላ ቤት እስከ ባለ 12 ፎቅ ህንፃ ባለቤት ሆነው አሉ የተባሉ የሀገሪቱን ቱጃሮች በሀብት በልጠው የሚንደላቀቁ መሆናቸው እየታወቀ ቀድመው ደምተዋልና ሊከሰሱ አይገባም ተብሎ ስማቸው እንዳይመዘገብ ቢከለክሉም ውሎ አድሮ ግን መጠየቃቸው አይቀሬ መሆኑን የህግ ባለሙያዎች በቁጭት ሲገልፁ ተደምጠዋል፡፡

ለስሙ መጪውን አምስት ዓመት በላቀ የዕድገት ጉዞ እንቀጥላለን፣ ድህነትን ከሀገር እናባርራለን፣ ልመናን ጨርሶ እናጠፋለን እያሉ ባዶ ጩኸት እየጮኹ ቢሆንም ይህንን ከልብ ተግባራዊ ለማድረግ በወሰኑ ኖሮ መጀመሪያ ከኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የነጠቁትን ሀብት እና ንብረት መልሰው ይቅርታ መጠየቅ ነበረባቸው ያሉት የህግ ባለሙያዎች ይህንን ባላደረጉበት ሁኔታ ልማት እድገት እያሉ ቢወተውቱ ለውጥም አይገኝ እነሱንም የሚያምን የለም ሲሉ ገልፀዋል፡፡

EthioLion.com